# እንተማመን

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

ማንም ይረዳዋል ብዬ እንደምገምተው መተማመን ከሌለ እንኳን አገርና ቤት ግንባታ ስርቆትም ከዳር አይደርስም። "ስርቆት ሳይሞክር አልቀረም!" እያላችሁ አትሳለቁብኝ እንጅ ሌቦችም የሰረቁትን እስከሚከፋፈሉና የሌብነት መረባቸው እስከተበጣጠሰ ጊዜ ድረስ ይተማመናሉ። እኔ እንደሚገባኝ ማንኛውም ህብረተ-ሰብ አብሮ በሰላም መኖር የሚችለው በህግ ሳይሆን በመተማመን ነው። በተለይ ህግ በማይሰራበት በኛ አገር ሰው ወጥቶ በሰላም የሚገባው በመተማማን ነው። አዎ ጦቢያዊ ገንዘብ ሆነ ሌላ እቃ የሚያበድረው ወይም የሚያውሰው በእምነት ነው። ጋብቻንም ሆነ ሌሎችን ውል የሚዋዋለው በመተማመን ነው። በሰይፍና በጎራዴ ታንክ የሚነዳና መርዝ የሚረጭ ወራሪ ጠላት ተዋግቶ አገርና ክብር የጠበቀው እጅግ በረቀቀ ወታደራዊ ሕግ ሳይሆን እምነት በሚባል የህሊና ሕግ በመመራት አብሮ እየዘመተ ነው። እንደአለመታደል መተማመን በጦቢያው ውስጥ እንደዛሬው ፈተና ውስጥ ወድቆ የሚያውቅ አይመስለኝም።

ታኦ ችንግ(Tao Ching) የተባለ ጥንታዊ ቻናዊ ፈላስፋ [1] እንዳለው *እምነት በሌሎች ላይ ያጣ ሰው ሌሎች በርሱ ላይ እምነት እንዲያጡ ያደርጋቸዋል።* ይህ አባባል በአፍሪካ ገዥዎችና ሕዝቦቿ በተለይም በጦቢያ እውን ሆኗል። ገዥዎች ሬሳ ተራምደው ከወንበር ጋ ቁጭ ስለሚሉ በሌሎች ላይ እምነት ያጣሉ። እምነት ማጣት ፍርሃትና ጭንቀት ይፈጥራል። ፍርሃትና ጭንቀት አረመኔ ያደርግና ልጅ አዋቂውን በባሩድ ያስፈጃል። በዚህ ምክንያት አረመኔ ገዥዎች በሕብ ዘንድ ተቀባይነትና ታማኝነት ማጣት ብቻ ሳይሆን ይጠላሉ። ታማኝነት ማጣትና መጠላት ደግሞ ፍርሃትና ጭንቀትን ከዚያም ኢሰብአዊነትን እያጎለበተ ሕዝብን በሰቆቃ የውህደት ቀለበት (vicious circle) ውስጥ ሲያሽከረክረው ይኖራል። በታኦ ችንግ እምነት ገዥዎች አራት አይነት ናቸው። እንደ ጥሩነትና መጥፎነታቸው ቅደም ተከል ይህን ይመስላሉ። *የመጀመሪያውን አይነት መሪ ህዝቡ መኖሩንም የማያውቀው፤ ሁለተኛው ህዝብ የሚወደውና የሚያመሰግነው፤ ሶስተኛው ሕዝብ የሚፈራው፤ አራተኛው ሕዝብ የሚጠላውና የሚታገለው ናቸው።* አበዛኛው የአፍሪካ ገዥዎች በተለይም ደግሞ በጦቢያ ላይ ያሉ ከንቱዎች ከየትኛው እንደሚመደቡ አንባቢ በሚገባ የሚረዳ ይመስለኛል። "የቡና ሲኒ እያዬ መጠንቆል ያዘ እንዴ?" አትበሉኝ እንጅ በሶስተኛውና በአራተናው አይነት ገዥዎች የሚገዛ ሕዝብ በምንም አይነት ታምር ከሰቆቃ፣ ርሃብ፣ በሽታና የአለም መሳለቂያ ከመሆን ሊድን አይችልም።

በአፍሪካ በተለይም በጦቢያ የሚገርመው ነገር ግን የገዥዎችና የሕዝቡ አለመተማመን ብቻ ሳይሆን እንዲህ አይነቱን አገዛዝ እንለውጣለን የሚሉት ቡድኖችም የርስ በርስ አለመተማመን ነው። አስታውሱ! በሌሎች ላይ እምነት ያጣ ሰው ወይም ቡድን ሌሎች ሰዎች ወይም ቡድንኖች እምነት እንዳይጥሉበት ራሱን ያጋልጣል። ይህ ማለት እነዚህ እርስ በርስ የማይተማመኑ ቡድኖች የተነሱበትን መጥፎ አገዛዝ የመለወጥ ወይም ፍትህ የማስፈን አላማ ይተውና እርስ በርሳቸው ጥርጣሬ ውስጥ ይገባሉ። ከላይ እንደተገለጸው ጥርጣሬ ፍርሃትና ጭንቀትን ይፈጥራል። ፍርሃትና ጭንቀትም የእምነትና የአላማ ተካፋይን ሳይቀር አሳልፎ ወደሚሰጥ አረመኔነት ይቀይራል። በሌላ አነጋገር እነዚህ "ለፍትህ ታጋይ ነን" የሚሉ ቡድኖችም በሂደት ሊታገሉ የተነሱትን አውሬ መስለው ቁጭ ይላሉ ማለት ነው። ታዲያ እንዲህ አይነቱ ክህደት ወይም መካካድ ዛሬ አልተጀመረም።

ዲያብሎስን ለመታገል ምሎ ክርስቶስንስ የተከተለው ይሁዳ (በታሪክነትም ሆነ በእምነት መልክ ልናየው እንችላለን) ከሰይጣን ሊያላቅቁት የተነሱለትን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ራሱን ክርስቶስን አሳልፎ ሰጥቷል። በተመሳሳይ መንገድ አንድ ምስራቃዊ ጸሐፊ [2] እንደጻፈው በአንድ ወቅት በኤሽያ ትልቅ ክብር ያላቸው የእስላም መሪ ሼህ ነበሩ። እኒህ ሼህ በደህናው ጊዜ ከአጠገባቸው የማይለዩ ስልሳ ተከታዮች(desciples) ነበሯቸው። በዚህኑ ወቅት እንደ ጦቢያ ሕዝብ ሁሉ ህዝባቸው በገዥዎች መከራን እየቀቀለ ይበላ ነበር። እኒህ የተባረኩ የነፍስ አባት(እኛ ስለሌለን በመቅናቴ አትፍረዱብኝ እንጅ ቀናሁ!) ከእለታት አንድ ቀን ተከታዮቻቸውን "ረጅም ጉዞ ልንጀምር ነውና ተዘጋጁ!" ይሏቸዋል። አያይዘውም በመጀመሪያ ግን ችግር ቢያጋጥመን (የራሳቸውን ስም እየጠሩ) ከርሱ በፊት እኔ እሞታለሁ እያላችሁ ለመናገር ቃል ግቡ ይሏቸዋል። ሼሁ ይህን እንደተናገሩ ሃምሳ ዘጠኙ በመጠራጠር ወዲያውኑ ከዱና ከአጠገባቸው ጠፉ። አንዱ ብቻ ቃል ገባና ተከተላቸው። ሁለቱ ረጅሙን ጉዞ ጀመረው ፍትህን ሲሰብኩ በአረመኔው ገዥ ተያዙና አረፉት። አረመኔው ገዥም መጀመሪያ ያንን ቃሉን ጠብቆ የተከተላቸውን አማኝ "ልገድልህ ነው!" ይለዋል። በዚህን ጊዜ መሪው ሼህ "በሱ ጥፋት የለምና እኔን ግደሉኝ!" ይላሉ። ተከታዩ አማኝም በበኩሉ በሼሁ ፋንታ እኔን ግደሉኝ እያለ መማጠን ጀመረ። (በነገራችን ላይ ልጅ ሆኜ እኔ ክንዴን ሳልንተራስ አትነካውም እያሉ እጉም ብሎ የተጠጋቸውን የማያውቁትን ሰው ሳይቀር ከደብዳቢ ወይም ከገዳይ የሚያድኑ ሰዎች አውቅ ነበር።) በዚህ አንዱ ለሌላው ሲል ራስን አሳልፎ መስጠት ግራ የተጋባው ገዥም ጥቅም ቢኖረው ነው እንዲህ ለመሞት የሚለማማኑት ብሎ በመገመት "በነሱ ፋንታ እኔን ግደሉኝ" ብሎ ወታደሮቹን አዝዞ በሃይማኖት መሪዎች ፋንታ

እርሱ ሞተ ይባላል። ይህ ማለት ሃምሳ ዘጠኙ ቢክዱም ሁለቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ፣ በእነርሱ እምነትና መተማመን ለሕዝብ መድህን ሆነዋል ማለት ነው።

በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደታየውና እንደሚታወቀው የጦቢያ ገዥዎችና ሕዝብ በጭራሽ የሚተማመኑ አይመስሉም። ሕዝቡም በቋንቋ ተከፋፍሎ እርስ በራሱ እንዳይተማመን እየተደረገ ነው። እንዲህ አይነቱን ጉድ እንቀይራለን ብለው ከአርባ አመታት በፊት ጀምሮ እስካሁን ድረስ የሚደራጁት ቡድኖችም እርስ በራሳቸው አይተማመኑም። እንኳን ሌላው የእስልምናም ህነ የክርስትና መሪዎች ነን የሚሉት ሰዎች እንኳን አይተማመኑም። በከሃዲነት፣ ስልጣን ወዳድነት፣ በነፍሰ ገዳይነት፣ በገንዘብ አባካኝነትና በሌሎችም የአስርቱ ቅላት ጥሰት ወንጀሎች ሲወነጃጀሉ ይደመጣሉ። ታዲያ መተማመን በጠፋበት በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ፍትህ እንዴት ብሎ ይሰፍናል? እግዚአብሔርስ እንዴት ብሎ ምህረትን ይልክልናል? ሕዝብስ አንገት ከሚያስደፉ እርሃብና በሽታ እንዴት ብሎ ይላቀቃል?

ሳጥናኤልና አረመኔ ገዥዎች በጋራ የሚፈሩት ጽኑ እምነትንና መተማመንን ነው። እንኳን አገር፣ ቤተክርስቲያንና መስጊድ የሚያህል ነገር ለመገንባት እቁብ እንኳን ለማቋቋም ወረቀት ላይ ከሚሰፍረው ደንብ ይልቅ መተማመን እጅግ ያስፈልጋል። በርግጥ ይህ ማለት ደህና ነገር ለማምጣት ሁሉም ሰው የግድ መተማመን አለበት ማለት ላይሆን ይችላል። እንደሚታወቀው ክርስቶስ ሁለት ሺህ ዘመን ሙሉ ባለም ላይ የተሰገደለትና ወደፊትም ሲሰገድለት የሚኖረው በራሱ በአንዱ ሰው መስዋእትነትና በጥቂት ህይወታቸውን አሳልፈው በሰጡ ስማቸው ዘላለም በሚወሳ ታማኝ ሃዋርያት አማካኝነት ነው። እኒያ ከላይ የተገለጹት የእስያ እስልምና ተከታዮችም ነጻ የወጡት በሃምሳ ዘጠኝ ከሃዲያን ሳይደናገጡ የፍትህ ስራቸውን በቀጠሉ ሁለት የእግዚያብሔር አማኞች እርስ በርስ መተማመን ነው። የጊዜ ጉዳይ እንጅ ጦቢያም ሕዝብ አምነው የሚታመኑ መሪዎች ወይም ሃዋርያት እንደማያሳጣት እምነቴ ነው። እስከዚያው ግን እኛም ገዥዎች የግፍ ዘመንን ለማራዘም በዘረጓቸው እምነት-አፍርስ ወይም የመከዳዳት መረቦች እየተጠለፍን የረባ ነገር ሳንሰራ እርስ በርስ ስንናከስ ኖረን ከማይቀረው መቃብረ ውስጥ ከምንገባ ተማምነንና አንድ ላይ ሆነን ፍትህን ፍለጋ ስንጓዝ ውሃም ቢሆን ቢበላን ለስጋም ለነፍስም የሚበጅ ይመስለኛል። አመሰግናለሁ!

*ዋቢ*


1. *Tao Tech Ching by John Wu page 35*

2. *The Thinkers of the East by Idries Shah page 25-27*


*ተመሳሳይ ጽሑፎች*

1. *ይድረስ ለእኛ* [www.quatero.net/meta/yidres.pdf](www.quatero.net/meta/yidres.pdf)
2. *ለመውደቅ ተውላጠ-ስም መደርደር ይብቃን!* [www.adisvoice.com/article/mewdek[1].pdf](www.adisvoice.com/article/mewdek[1].pdf)